Resource-Orientated Sanitation concepts for peri-urban areas in Africa

# የሰው ሽንትን ለእጽዋት

# ማዳበሪያነት መጠቀም



**የሽንት አቀማመጥ መመሪያ**

- ከአንድ ቤተሰብ የተሰበሰበ ሽንት ወዲያው ወይም አጭር ግዜ ካስቀመጡ በኋላ ቤተሰቡ ለሚጠቀምበት ሰብል አገልግሎት ላይ ማዋል ይቻላል ::
- ከተለያየ ቤተሰብ የሚሰበሰብ ሽንት ከሆነ
  ለከብት መኖ ማዳበሪያ ከአንድ ወር በላይ
  ለምግብ አገልግሎት የሚውል ሰብል ከሆነ

ለስድስት ወር ከመጠቀም በፊት ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

- ሽንት ከፕላስተኪ ወይም ከብርጭቆ ከተሰሩ እቃዎች ውስጥ ግጥም ተደርጎ መቀመጥ አለበት፡፡

**በሽንት ወስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮች**

በአማካይ በሽንት ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮች መጠን የሚከተለው ነው፡፡
ናይትሮጅን 4–5 ግራም በሊትር
ፎስፈረስ 0.5–1 ግራም በሊትር
ፖታሲዬም 1.5–2 ግራም በሊትር
ድኝ 1.5–2 ግራም በሊትር



ስለዚህ ሽንት ዩሪያና ዳፕ ማዳበርያዎችን ሊተካ ይችላል ማለት ነው፡፡
እንደ ሰብሉ አይነት ከፍተኛው አጠቃቀም በግምት 120 ኪሎ ግራም ናይተሮጅን በሔክታር በአመት ነው፡፡ ስለዚህ 2.5-3 ሊትር ሽንት በእያንዳንዱ ካሬ ሜትር ከፍተኛው የሽንት አጠቃቀም ነው፡፡

**ሽንት አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችልባቸው የሰብል አይነቶች**

<u>ለምሳሌ</u>

በቆሎ፣ቲማቲም፣ጤፍ፣ባቄላ፣በርበሬ፣ኤግ ፕላንት፣ጥጥ፣የፍራፍሬ ዛፍ፣ ወዘተ…
በጠቅላላው ሽንት ናይትሮጅንን በከፍተኛ ሁኔታ ለሚፈልጉ ዕፅዋቶች አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል፡፡



**ተጨማሪ የሽንት አገልግሎት**

- ሽንት የኮምፖስት ዝግጅትን ያፋጥናል
- ሽንት የዕጽዋት ቅሬት ለማብላላት የሚውል ጥሩ ሜዲያ ነው



**ለተጨማሪ መረጃ**

world health organization (2006)፡ guidelines for the safe use of waste water excreta and gray water

ሮዛ ቢሮ አርባ ምንጭ
ፖ.ሣ.ቁ. 40 <u>አርባ ምንጭ</u>
አርባ ምንጭ ዩንቨርስቲና
አርባ ምንጭ ከተማ ውሃ አገልግሎ
& ስልክ 251 (0) 46-8815115
e-mail = kinfe_k@yahoo.com
web-http;//rosa.boku.ac.at

## ሽንትን እንደማዳበርያ የምንጠቀመው ለምንድን ነው?

ሽንት ዕጽዋት ለእድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ይዟል፡፡
ዕጽዋቶች የንጥረ ነገር ፍላጎታቸው ይለያያል፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ ሽንት ጠቃሚ የእጽዋት ንጥረ ነገሮችን ስለያዘና ሽንት በነጻ ስለሚገ„ ለማዳበርያ መግዢያ የሚወጣውን ወጪ ይቀንሳል፡፡

## ሽንትን እንዴት መሰብሰብ ይቻላል?

ሽንት ሽንትን ከሰገራ በሚለይ ሽንት ቤት ወይም ለወንዶች ለሽንት መሽኛ ብቻ ተብለው በተሰሩ ዩሪናል ወይም ለሴቶች ብቻ ተብለው በተሰሩ ኢኮሊሊ መሰብሰብ ይቻላል፡፡ ስእሉን ከታች ይመልከቱ





## በሽንት ውስጥ ጎጂ ነገሮች አሉን ?

ሙሉ ለሙሉ ለማለት ይቻላል በሽታ አምጪ ሕዋሳት ያሉት በሰው አይነ ምድር ውስጥ ነው፤ ስለዚህ አይነ ምድር ከሽንት ጋር እንዳይቀላቀል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል በተጨማሪም ሽንትን ለተወሰኑ ቀናት ማስቀመጥ ይህንን ችግር ይቀንሰዋል፡፡
HIV/AIDS በሽንት አይተላለፍም፡፡
ጨዋማ የመሬት ችግር ያለባቸው መሬቶች ላይ ሽንትን መጠቀም ሁኔታውን ያባብሳል፡፡


## ሽንትን ለማዳበርያ የመጠቀም መመሪያ፡

- ሽንት ከውሃ ጋር ተደባልቆ ወይም ሳይደባቅ እርሻ ላይ መጠቀም ይቻላል
- ሽንትን ለመታጨድ አንድ ወር በቀረው ሰብል ላይ መጠቀም አያስፈልግም
- ሽንት ቀጥታ የእጽዋት ቅጠሎችን እንዳይነካ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል
- በሽንት ውስጥ ያለው ጠቃሚ ነገር በትነት መልክ እንዳይጠፋ በጠራራ ፀሐይ ሽንትን መጠቀም አያስፈልግም
- ሽንትን ወደ መሬት አቅርቦ ማጠጣት ያስፈልጋል
- ሽንት ከተጨመረ በኋላ በአፈር መሸፈን ያስፈልጋል
- በሽንት ውስጥ ያለውን አሞንያ የተባለውን ንጥረ ነገር ወደ መሬት እንዳይሰርግ ብዙ ሽንት በአንዴ መጠቀም ወይም በከባድ ዝናብ ወቅት መጠቀም አያስፈልግም፡፡
- ሽንት ወራጅ ውሃ ወይም ኩሬ በቅርብ ባለበት አካባቢ መጠቀም አያስፈልግም፡፡



**የሽንት አጠቃቀም መመርያ**
ለአንድ ሰብል የሚያስፈልገውን የሽንት መጠን ካወቁ በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ሶስትና አራት ከፋፍሎ ማጠጣት ይቻላል፡፡
***አንደኛ መጨመር ያለበት፡*** እህል ከመዘራቱ በፊት

***ለሁለተኛ ጊዜ መጨመር ያለበት፡*** ከ2-4 ሳምንታት ሰብሉ ከተዘራ በኋላ (በውሃ 1፡3 _1፡5 መደባለቅ ይቻላል)
***በመጨረሻ መጨመር ያለበት***
እህል ከመታጨዱ አራት ሳምንት በፊት ወይም የእድገቱ 2/3 እስከ ¾ እንዲዳረስ፡፡

## ምን ያህል ሽንት እንደ ማደበሪያ መጠቀም እንችላለን?

ሽንትን ለማዳበሪያ ስንጠቀም አጨማመሩ ሽንት ውስጥ ባለው ንጥር ነገር እና እንደ እጽዋቱ የንጥረ ነገር ፍላጎት ይወሰናል፡፡

በሽንት ውስጥ ያለው ናይትሮጅን መጠን ካልታወቀ፡ በአጠቃላይ ከ 1እስከ 2 ሊትር ለአንድ ካሬ ሜትር በአንድ የእህል መዝሪያ ወቅት መጠቀም ይቻላል፡፡

- ½ ሊትር ለብርእ ሰብሎች ለአንድ እግር
- ¼ ሊትር ለጓሮ አትክልቶች በአንድ እግር
- 1-3 ሊትር በወር ለትንንሽ ዛፎች ለአንድ እግር
- 3–6 ሊትር በወር ለትልልቅ ዛፎች በአንድ እግር